# ተስፋ ከሌለበት ተስፋ ፍለጋ!!


## ጌድዮን በቀለ

## Gedionbe56@yahoo.com


መንግስትና ህግ በፈረሰበት አገር "ባስቸኳይ አዋጅ" ስም የወያኔን ቅኝ ግዛታዊ ጭፍጨፋና አፈና ስርአት ለማስቀጠል የተጠነሰሰውን ሴራ፤ ተከትሎ ይሆናል - አይሆንም "ፓርላማ" ያጸድቀዋል አያጸድቀውም ሲባል የተከረመበት ሙግት ቢያንስ የወያኔን አላማና አደረጃጀት ባህሪ ጠንቅቀው በሚረዱት ወገኖች በኩል የገሙቱት ሆኖ ቢገኝም፤ ከወያኔ ጓዳ ሙጥቅላም ብትሆን "ተስፋ" ትኖራለች ብለው ለሚጠባበቁ ወገኖቼ ግን የመጨረሻ ሊሆን የሚገባ መልስ ያስገኘ ይመስለኛል።

ተስፋ ከሌለበት ሲጠበቅ የነበረው ተስፋ የተጀመረውን ህዝባዊ ትግል ደረጃና አቅጣጫ ከማመላከት የዘለለ እርባና ያለው ውጤት እንደማያመጣና በዚህም የተነሳ መዘናጋት እንደማይገባ ለማሳሰብ ሃሳብ ብልጭ ብሎብኝ ሳለ፤ ሃሳቤን ካይምሮዬ አውርጀ ከወረቀት አገናኝቸ ሳላበቃ ሊሆን የታቀደው ድራማ በታቀደለት ደረጃም ባይሆን ይሆናል በተባለበት መንገድ ተፈጠመ፤ ከእነ ነውሩ፤ ከእነ አጸያፊ የታሪክ ገጽታው ።

ለተስፋ ሰናቂዎቹ ወዳጆቼና ከነሱ ጎን ተሰልፈው በየጊዜው ወያኔ የሚወረውራትን ኳስ እየተቀበሉ ወደሰማይ በማጎን የሚያጫጩሁን "የፖለቲካ ተንታኞች" ይህም ሌላ መማሪያና መለበሚያ ከሆናቸው "ከመናገራችን በፊት ደግመን ደግመን ማሰብ" የሚለውን የነገር አዋቂዎች አባባል የሚያጤኑበት እድል ሰጥቶ አልፏል ብዬ አስባለሁ።

ለምሳሌ ድንገት ተነስተው አባዱላን የመሰለ "ምስለ-ሰው" እንኳን ለተወለደው በቴለቪዥን መስኮት ለሚያውቀው አንገት የሚያስደፋ የሞት አዋጅ አስፈጻሚ ሆኖ ሲያገኙት "ስለጣኔን በፈቃዴ ለቅቄያለሁ" በማለቱ ብቻ በብርሃን ፍጥነት " ከቄሮ አደረጃጀት ጀርባ ያለ "ስውር መሪ" "ጥልቅ ፖለቲካዊ ብልሃት ያለው፤ በህቡእ የፖለቲካ አስኳል አደረጃጀት የላቀ ልምድ ያለው " ምንትስዮ ምንትስዮ እያሉ የተከለሰውነት አምበረጭቃ ከመለቅለቅ ሊቆጠቡና ሌላ ጽንፋዊ ስተት ከመስራት ይታቀባሉ የሚል ተስፋ አለኝ።

ቀደም ብሎ ወቅታዊነቱ ገና ጸሃይ ሳይሞቀው በከሸፈው ጽሁፌ ላይ ፤" በርካቶች እንደተመኙት "ነፍስ-አልባው ፓርላማ" ነፍስ ዘርቶ ከኔ በተቃራኒ ተስፈኞች ተስፋ ባደረጉበት አቅጣጫ ቢወስንና እኔን ስህተተኛ ቢያደርገኝ ምንኛ ደስ ባለኝ ፤!! ተስፋ ከተቆረጠበት የሚመነጭ ተሰፋ እንደተአምር ይቆጠራልና ለማለት ተዘጋጅቸ ነበረ ።

የ"ፓርላማ ተበዬው" አስነዋሪ ድራማ ውጤት ታዲያ እኔንም ሆነ ቅን አሳቢ ወዳጆቼን አጋርቶን ተጠናቀቀ። ባንድ በኩል ከምስለ-ሰዎች ስብስብ መሃከል ነፍስ ያላቸው 88 ተቃዋሚዎች፤ 7 ድምጽ ነፋጊዎች 107 አልተመቸንም ባይ አልምጦች ብቅ በማለታቸው አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ጀግኖች በማለት ከጉልበቴ ሸብረክ ከወገቤ ዝቅ ብዬ እጅ ስነሳ በሌላ በኩል ባልሳሳት "346? ምስለ-ሰው " የእንግዴ ልጆችን ሹግ የመሰሉ እጆችን መመልከት ደግሞ የሚያሸማቅቅ ቢሆንም ግምቴና ውጤቱ መሰረት እንደነበረው አረጋግጦልኛል።

ቀድሞውንም ቢሆን የግድያው አዋጅ ከተጻፈበትና ከተሰራጨበት ቀናት አስቀድሞ በስራ ውሎ ሳለ ስለምን ድራማው አስፈለገ? የሚለውን ለመመለስ የወያኔን ማንነትና በዙሪያው ያሰለፋቸውን ፈረሶች ምንነት ማወቅ በቂ ይመስለኛል።

መላምት አንድ፡ ወያኔ እጅግ ከመጠን ያለፈ ነውር የለሽ፡ ውሸታምና የሌባ አይነ ደረቅ ነው። ስለዚህ ህግ በሌለበት ህጋዊ፡ ፍትህ በማይታወቅበት ፍትሃዊ ነኝ በማለት የተካነ ከድንቁርናና ከለክዬለሽ አምባገነናዊ ንቀት የተገነባ ቡድን ነው።

መላምት ሁለት ፡ ወያኔ የሰራውን የይስሙላ ህግ አፈራርሶ ራሱን ህግ ያደረገ ቡድን በመሆን ስልጣን በጉልበት የነጠቀ ቡድን በመሆኑ ተጠሪነቱ ለራሱና የዶላር ፍርፋሪ ለሚያቃምሱት መንግስታት ብቻ ነው፤ ስለሆነም የሚፈራቸው አበዳሪዎችና ፍርፋሪ የሚያቃምሱ ጌቶቹ ፊታቸውን እያዞሩበትም እንኳ ቢሆን አይኑን በጨው አጥቦ ለመቅረብ የዳዳበት ነው።

መላምት ሶስት፡ ለወያነ "ኢህአዴግ" የተሰኘው ቡድን የተሰራው "በነጻ አውጭነት" ጭንብል የተደራጀበትን ህዝብን ከህዝብ በማጋጨት ያለርህራሄ የሚፈጽመውን የዘረፋ ስራ ለማስፈጽም የሰራው "የትሮይ ፈረስ" እንደመሆኑ ማንም ያሻውን ትርጉም ቢሰጥ ፈረሱ የሴራው ዋና አስፈጻሚ መሆኑን ለማስረገጥና በፈረስነት የሚጋልባቸው "ፓርላማ ተብዬ" ምስለ ሰዎችን የወንጀሉ ተባባሪ በማድረግ ከመጡበት ህዝብ ለመነጠል ነው። በዚህ ደግሞ ወያኔ ለሚቀጥሉት ጊዜያቶችቹ ስነ-ልቦናቸውና ቅስማቸው የተሰበሩ እንዳሻው የሚጋለባቸው "ምስለ-ሰው " ጉዳይ አስፋጻሚዎች ይኖሩታል።እንግዲህ በነዚህና ሌሎች ተጨማሪና ተያያዥነት ባላቸው መላምቶች የተነሳ "የፓርላማ-ተብየው" ድራማ አሰፈላጊ ሊሆን ችሏል።

ይህን ተከትሎ ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ የተጀመረው ህዝባዊ ትግልና ትቃውሞ ተጠናክሮ እንዲቅጥልና ሊከተል የሚችለውን አደጋ ለመቀነስ መወሰድ ስለሚገባው ጥንቃቄና የትግል አቅጣጫ ጉዳይ ነው።

ከሁሉም የሚቀድመው የነፍስ ገዳዩን ቡድን መሰሪነት በቅጡ መረዳትና ከዚህ መሰሪ ቡድን የሚመነጭ ቅንጣት በጎ ሃሳብ ወይም እርምጃ ሊኖር እንደማይችል በመገንዘብ የሚወረውርልንን የመጫዎቻ ካርዶች በጥንቃቄ መርምሮ በራሱ ካርድ ማሸማቀቅን መለማመድ ዋናው ጉዳይ ነው። ባጭሩ በማናቸውም ጊዜና በማናቸውም ጉዳይ ከወያኔ በተቃራኒ ማሰብና ያንንም ተግባራዊ ማድረግ። ለምሳሌ ወያኔ የሚጠላቸውን መውደድ፤ የሚያዋርዳቸውን ማክባበር፡ መልስ የሚፈልግባቸውን መንፈግ የመሳሰሉት ላይ ማተኮር ይሆናል።

ከፊታችን ያለው ውነት የሚያስገነዝበን፤ ወያኔ ለጊዜውም ቢሆን ለ27ዓመታት "በህጋዊነትና ህገመንግስታዊ ስርዓት" ስም ሲያጭበረብርበት የነበረውን ጭንብል ታሪክና ትውልድ ወደፊት ባክብሮት በሚዘክራቸው ቄሮዎች፡ ፋኖዎች፤ ዘርማዎችና ነጻነት ናፋቂ ኢትዮጵያውያን ትግልና መስዋእትነት አውልቆ እንዲጥል መገደዱን ነው።

ሌላው ውነት ከዚህ ወዲያ ወያኔ "መንግስት" (ድሮም መንግስታዊ ባህሪ ባይኖረውም) ሳይሆን ወራሪ መሆኑን ከልብ መቀበል ነው። ትናንት አባይ ፀሃዬ፡ አቦይ ስብሃት፡ የኮምኒኬሽኑ ዘርኣይና ጌታቸው ረዳ ደጋግመው እንደነገሩን " ወያኔ የያዘውን ወሳኝ የፖለቲካ ኢኮኖሚያዊ፤ ወታደራዊና የደህንነት ጅምላ ባለቤትነት ከሚያጣ" "ኢህአዴግ" የተሰኘውን የትሮይ ፈረሱን ቢገድው እንደሚመርጥ ነው። ሌላው ወገን አልሰማ አለ ወይም ሰምቶ አልዋጥልህ አለው እንጅ ወራሪዎቹ "ነጻ አውጭዎች" ዛሬም ያሉት በጠላት ወረዳ ውስጥ ነው። ጠላት ደግሞ መጥፋት አለበት ስለዚህ በጠላትነት የፈረጁዋቸውን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ለማጥፋት ቆርጠው ተነስተዋል ።

በጭካኔ በግፍና፤ በቅኝ ገዥነት ወኔ ረግጦ ለመግዛት ቆርጦ የተነሳው ይህ አናሳ ቡድን ይህንኑ አላማውን ለማስፈጸም በትጋት፡ በጭካኔና በማናለብኝነት መሰለፉን ተገንዝቦ በተቃራኒው የዚህን ቡድን ዓላማ ለመቃወም የተሰለፈው ወገን ከስሜታዊነት፤ ካጉል "የእንትን ..እንትን ይወድቅ ይሆናል .." ከሚል ቀቢጸ ተስፋ ወጥቶ ፤ በህዝብ አስግዳጅነት ተገፍተውና ተወጥረው ከወያኔ ጎራ ማፋግፈግ የጀመሩ ግለሰቦችን የልብ ትርታ እያዳመጠ የወግ ደንገላሳ ከመደንከር ተገትቶ፤ በኢትዮጵያውያን ወጣቶች አርድ አንቀጥቅጥ ትግል አፋፍ ላይ የደረሰው የነጻነት ቀን ዋዜማ እንዳይታጠፍ የሰከነና የተጠና ድጋፍና የመፍትሔ ፍሊጋ አቅጣጫ በማመላከት ስራ ሊጠመድ ይገባዋል።

ለምሳሌ "እኛን የነካ ትግራዊን ነካ!" የሚለው ጩኸት በተጻራሪ ለቆመው ወገን ዋና የማወዛገቢያና የመነጋገሪያ አጀንዳ እንደሚሆን ፊደል ዳገታቸው ለሆኑት ጥቂት ወሮበሎች አልመውና አስበው የሚመዙት መጫዎቻ ካርድ ነው። ለነሱ በዚህ ካርድ ሰበብ ሊከተል የሚችለው አደጋ ጉዳያቸውም አይደለም፤ ይልቁንስ እነዚህ በነፍጥ ጀርባ ተደብቀው ከመግደልና ከመዝረፍ የዘለለ እውቀት የላቸውም የሚላቸው ፊደል ያነበበ ወገን "በመልስ እሰጥ ባይነት " ሲንጫጫና ሲብከነከን በግዴለሽነት የወረወሯት ካርድ የታሰበላትን ግብ መምታቷን ማየት ነው ዋና ግባቸው። እንዲህ ለመሳሰለው ወያኔ ለሚመዘው ካርድ መልስ መስጠት የጨዋታውን አቅጣጫ በማስቀየር ለተካነው ወያኔ ሰርግና ምላሽ ወይም አፈር ልሶ ከሞት የሚነሳበት ምሱ ነው። ዝምታ ወይም በተቃራኒው ማስብ ግን እስትንፋሱን የሚያሳጥር ግባተ-መሬቱን የሚያቃርብ የጅል የሚመስል ጥልቅ ብልህነት የተሞላበት የትግል ስልት ነው። መልስ መስጠት ቢያስፈልግ እንኳ "አሉታዊም ይሁን አዎንታዊ" መልሱን እንዲሰጥ የሚጠበቀው "በስሙ የሚጉራሩበት ወይም የሚመጻደቁበት ትግራዊ ማህበረሰብ ሊሆን ይገባዋል።

ከዚያ በተረፈ ሌላው ወገን የሚሰጠው ምላሽ የጨዋታውን የበላይነት ከማስነጠቅ የዘለለ ፖለቲካዊም ሆነ ማህበረሰባዊ ፋይዳው እምብዛም ነው ። ሌላው የቅርብ ጊዜ ተጨባጭ ማስረጃ " የኦሮሞ ደም ደሜ- ያማራ ደም ደሜ " የሚለው ያማራና ኦሮሞ ወጣቶች የትግል ስልት ነው። ሁላችንም እንደምናውቀው በዚህ መፈክር የተነሳ በወያኔ ካምፕ የተፈጠረው መተራመስና ሽብር እስከዛሬ ቀጥሎ ፤ የደረሰበትን ያንጀት ነቀርሳ ሊፈውስበት የሚያስችል ሰይጣናዊ መድሃኒት ሊያገኝለት ባለመቻሉ ከቀን ወደ ቀን ወደ ፍጻሜ ዘመኑ እየተቃረበ ይገኛል።

በሌላ በኩል በኦሮሚያ እየተካሄደ ባለው የቁሮ አይበገሬ ህዝባዊ መነሳሳት በመገፋት ወይም ከራሳቸው ልቦና በመነጨ ቁርጠኛነት ለትግሉ መነቃቃት ጉለህ አስተዋጾኦ በማድረግ ላይ ያሉት የለማና አብይ ቡድኖች ባንድ በኩል በወያኔ ከተደገሰላቸው የቀረጣ ምት ለማምለጥ በሌላ በኩል በከፍተኛ ደረጃ የተጀመረው የተጠናከረ ጭፍጨፋ፤ አፈናና አባሎቻቸውንና የህዝብ ተወካዮችን የማሰር ዘመቻ እንዲገታ የተናደና የፈረሰም ቢሆን እንኳ " በህገመንግስቱ" የተሰጣቸውን ክልላቸውን የማስተዳደር መብት የፌደራሉ መንግስት እንዲያከብር በመግለጫ ለህዝብ በማሳወቅ ለጥያቄያቸው ተፈጻሚነት ህዝቡ ከጎናቸው እንዲሰለፍ አስቸኳይ ጥሪ ማድረግ እንደሚገባቸው ማስገንዘብ ሌላኛው የትግል ስልት ሆኖ ሊወሰድ ይገባል።

"በጸሎት ዓለማየሁ" የተባሉ ጸሃፊ ከአሜሪካዊው ፓትሪክ ሔነሪ ጋር በማነጻጸር አባይ ሚዲያ ላይ የጠቀሱትን አባባል ልዋስና በኦሮሚያና በደቡብ አንዳንድ አካባቢዎች የተጀመረው "ነጻነቴን ወይም ሞቴን ስጡኝ" ትግል የአማራውን ክልል ጨምሮ በሌሎቹ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ጋምቤላ፤ አፋርና ቤንሻንጉል እንዲስፋፉ መጣጣር ለሁሉም ነጻነት ናፋቂ ኢትዮጵያዊ የሚሰጥ የውዴታ ግዴታ ሊሆን ይገባል።

"ያለነጻነት ከመኖር ሞት ይመረጣል!!"